## ትምህርት 67

1. በጌቴሴማኒ የአትክልት ፍራየሱስ እጅግ ስለ ተጨነቀ መፀለይ ጀመረ፤ ኢየሱስ እጅግ የተጨነቀው ለምን ነበር?
ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ ከፊቱ ያለው ሥቃይ ከዚያ በፊት ማንም ሰው ያልቀመሰው እጅግ አሠቃቂ መሆኑን ስላወቀ ነው።

2. ኢየሱስን ለመያዝ ሰይፍና ዱላ የያዙትን ሰዎች ይመራ የነበረው ማን ነበር?
ሀ- ይሁዳ።

3. ይሁዳ ኢየሱስን እንዲያስይዝ የመራው ማን ነበር?
ሀ- ሰይጣን።

4. በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን ማንን እየመራ ነው?
ሀ- ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ማመን የማይፈልጉት ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ይመራሉ።

5. የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሸሹት ለምንድን ነው?
ሀ- ደቀመዛሙርቱ የሸሹት ስለ ፈሩና ኢየሱስ የተያዘበበትን ምክንያት ስላልተረዱ ነው።

6. ደቀ መዛሙርቱ ያልተረዱት ነገር ምን ነበር?
ሀ- ደቀ ሙዛሙርቱ ኢየሱስ ከተያዘና ከተገደለ በኋላ እንዴት አዳኝ መሆን እንደሚችል አልተረዱም።

7. ኢየሱስን የያዙት ሰዎች ወዴት ወሰዱት?
ሀ- ኢየሱስን የያዙት ሰዎች ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰዱት።

8. የአይሁድ መሪዎች እንዴት በኢየሱስ ላይ ምንም ስሕተት አላገኙም?
ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ አንድም ስሕተት ስላልሠራ።
ለ- ምክንያቱም ኢየሱስ ምንም ኃጢአት ስላልሠራ።

9. ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስን “የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን?” ብሎ ሲጠይቀው ኢየሱስ ምን መለሰለት?
ሀ- ኢየሱስ «አዎ ነኝ፤ የሰው ልጅ በኃያሉ ቀኝ ተቀምጦ በደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ?» አለው።

10. ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስ መገደል አለበት ያለው ለምን ነበር?
ሀ- ሊቀ ካህናቱ አየሱስ መገደል አአበት ያለው እግዚአብሔርን ሰድቦአል ብሎ ነው።

11. ኢየሱስ እግዚአብሔርን ሰድቦአል?
ሀ- አልሰደበም።

- ሊቀ ካህናቱና የኢይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ ከፈረዱበት በኋላ ወደ ጲላጦስ መሩት።

ማርቆስ 15፡1

1- ጠዋት በማለዳ የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎች፥ ከጸሓትና ከመላው የሸንጎ አባላት ጋር ወዲያው ከተማከሩ በኋላ ኢየሱስን አስረው ወሰዱት፤ ጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት።

- ጲላጦስ ማን ነበር?

- ጲላጦስ በሮማው ንጉሥ በቄሣር የተሾመ የይሁዳ ገዢ ነበር።

- አይሁድ ኢየሱስን ለመግደል ከጲላጦስ ዘንድ ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው።

- ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት በቀረበበት ጊዜ ጲላጦስ ኢየሱስን አንድ ጥያቄ ጠየቀው።



- ከዚያም ዮሴፍ የኢየሱስን ስጋ ወስዶ በራሱ መቃብር ውስጥ ቀበረው።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው አዳኙ ከሀብታሞች ጋር ተቀበረ።

## ማርቆስ 15፥40-41

40- በዚህ ጊዜ ሴቶች ከሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር፤ ከእነርሱም መካከል መግደላዊት ማርያም፥ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም፥ እንዲሁም ሰሎሜ ነበሩ፤

41- እነዚህ ሴቶች በገሊላ ሲከተሉትና ሲያገለግሉት የነበሩ ናቸው፤ ደግሞም አብረውት ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ሌሎች ብዙ ሴቶች ነበሩ።

- እነዚህ ሴቶች በእግዚአብሔር ያመኑና ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ያወቁ ነበሩ።

## ማርቆስ 15፥42-46

42- ጊዜው እየመሸ መጥቶ የሰንበት ዋዜማ ይኸውም የመዘጋጀት ቀን ሆነ።

43- የተከበረ የሸንጎ አባልና የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ የነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ በድፍረት ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው።

44- ጲላጦስም እንዲህ በቶሎ መሞቱን ሲሰማ ተደነቀ፤ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ምን ያህል ጊዜ እንደ ሆነ ጠየቀው።

45- መሞቱንም ከመቶ አለቃው ካረጋገጠ በኋላ ሥጋውን ለዮሴፍ ሰጠው።

46- ዮሴፍም በፍታ ገዛ፤ ሥጋውንም አውርዶ በበፍታው ከከፈነው በኋላ፥ ከዐለት በተወቀረ መቃብር አኖረው። የመቃብሩንም ደጃፍ በድንጋይ ገጠመው።

- የአርማትያሱ ዮሴፍ ሀብታም ሰው ሲሆን አየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ያምን ነበር።

- ኢየሱስ ከሞተ በኋላ ዮሴፍ ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ስጋ ለመቅበር ለመነ።



## ማርቆስ 15፥2

2-ጲላጦስም፥ «አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?» ሲል ጠየቀው፤ ኢየሱስም፥ «አንተው አልኸው» በማለት መለሰለት።

- ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ ያለው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ የንጉሥ ዳዊት ዘር ነበር።

## ማርቆስ 15፥3-5

3- የካህናት አለቆችም በብዙ ነገር ከሰሱት።

4-ጲላጦስም፥ «ለምን መልስ አትሰጥም? እነሆ በብዙ ነገር ከሰውሃል» ሲል እንደ ገና ጠየቀው።

5-ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰም፤ ጲላጦስ ተገረመ።

- ሰዎች በሐሰት ኢየሱስን ቢከሱትም ኢየሱስ መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው አዳኙ በሐሰት ሲከሰስ ዝም አለ።

- በፋሲካ በዓል ወቅት ጲላጦስ ሁልጊዜ ለአይሁድ አንድ እሥረኛ የመልቀቅ ልማድ ነበረው።

- ስለዚህ ጲላጦስ አይሁድ ኢየሱስን ቢፈታላቸው ይወዱ እንደ ሆነ ጠየቃቸው።

## ማርቆስ 15፥6-11

6- በበዓል ሕዝቡ እንዲፈታላቸው የሚጠይቁትን እሥረኛ የመልቀቅ ልማድ ነበር።

7- በዐመፃ ተነሣሥተው ነፍስ ከገደሉ ዐመፀኞች ጋር የታሰረ በርባን የሚባል አንድ ሰው ነበረ።
8- ሕዝቡም መጥተው እንደ ተለመደው እንዲያደርግላቸው ጲላጦስን ለመኑት።
9- ጲላጦስም፥ «የአይሁድን ንጉሥ እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁን?" ሲል ጠየቃቸው፤
10- ምክንያቱም የካህናት አለቆች ኢየሱስን አሳልፈው የሰጡት በቅናት መሆኑን ያውቅ ነበር።
11- የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ ምትክ እንዲፈታላቸው እንዲጠይቁ ሕዝቡን አነሣሡ።

- ጲላጦስ ኢየሱስ ምንም ስሕተት እንዳልፈጸመ ያውቃል።

- ጲላጦስ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን የያዙት በቅንዓት መሆኑን ያውቃል።

- ስለዚህ ጲላጦስ አይሁድ ኢየሱስ እንዲፈታላቸው ይመርጣሉ ብሎ ተስፋ አደረገ።

- የካህናት አለቆች ግን ሕዝቡ በኢየሱስ ፈንታ ነፍሰ ገዳዩ በርባን እንዲለቀቅ እንዲጠይቁ ሕዝቡን አነሳሱ።

-ከዚያም ጲላጦስ አይሁድን አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው።

ማርቆስ 15፡12-14

12- ጲላጦስም እንደ ገና፥ «እንግዲያውስ የአይሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን እንዳደርገው ትፈልጋላችሁ?» አላቸው።
13- እነርሱም እንደ ገና፥ «ስቀለው!» እያሉ ጮኹ።
14- ጲላጦስም፥ «ለምን? ምን የፈጸመው ወንጀል አለ?» አላቸው። እነርሱ ግን፥ «ስቀለው!» እያሉ የባሰ ጮኹ።



- መጋረጃው የምን ምልክት ነበር?

- መጋረጃው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መለያየት ምልክት ነበር።

- እግዚአብሔርና ሰው የተለያዩት ለምንድን ነው?

- በኃጢአታችን ምክንያት።

- በኃጢአታችን ምክንያት እግዚአብሔርና ሰው ተለያዩ ከዚህ የተነሣም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ ከሊቀ ካህኑ በስተቀር ማንም መግባት አይችልም ነበር።

- በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረውን መጋረጃ ከላይ እስከታች የቀደደው ማን ነው?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር መጋረጃውን ለምን ለሁለት ቀደደው?

- ኢግዚአብሔር መጋረጃውን ለሁለት የቀደደው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ከእንግዲህ መለያየት እንደማይኖር ለማሳየት ነው።

ማርቆስ 15፡39

39- በኢየሱስ ትይዩ ቆሞ የነበረውም የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን ሲሰጥ ባየ ጊዜ፥ «ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር» አለ።

- የመቶ አለቃው ኢየሱስ መሞቱን ባየ ጊዜ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አወቀ።

- እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ ለምን ያህል ጊዜ አብረው ነበሩ?

- ለዘላለም።

- እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ አብረው ያልነበሩበት ጊዜ ነበር?

- አልነበረም።

- ይህ እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ አብረው ያልነበሩበት የመጀመሪያው ጊዜ ስለ ነበር ኢየሱስ ጮኸ።

- ከእግዚአብሔር አብ መለየት በዚህ ዓለም ላይ እጅግ አስፈሪ ቅጣት ነው።

ማርቆስ 15፡37

37- ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፥ ነፍሱን ሰጠ።

- ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ።

- ኢየሱስ ከሞተ በኋላ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ምን ሆነ?

ማርቆስ 15፡38

38- የቤተ መቅደሱም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ።

- በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረው መጋረጃ ሥራው ምን ነበር?

- መጋረጃው በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኙትን ሁለት ክፍሎች ይለያያል።

- መጋረጃው ቅድስትን ከቅድስተ ቅዱሳን ይለያል።



- ኢየሱስ ምንም ጥፋት ባይሠራም ሕዝቡ ኢየሱስን ስለጠላው እንዲሰቀል ፈለገ።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው አዳኙ ያለ ምክንያት ተጠላ።

- ሕዝቡ ኢየሱስን ለመስቀል ፈለገ።

- መሰቀል ምንድን ነው?

- መሰቀል የሰዎችን እጆችና እግሮች በእንጨት ላይ ቸንክሮ እስኪሞቱ ድረስ እዚያው መስቀሉ ላይ መተው ነው።

- መሰቀል ሮማውያን ከባድ ወንጀለኞችን የሚቀጡበት አሠቃቂ የሞት ቅጣት ነው።

- ከዚያም ጲላጦስ ኢየሱስ እንዲገረፍ አዘዘ።

ማርቆስ 15፡15

15- ጲላጦስም ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት ሲል በርባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠው።

- ሮማውያን አንድን ሰው ሲገርፉ ሹል የሆኑ ልዩ ልዩ የብረትና የአጥንት ቁርጥራጮች ያሉበትን ጅራፍ ይጠቀሙ ነበር።

- ሮማውያን ሰዎችን ሲገርፉ የሰዎቹ ጀርባ በጣም ስለሚቆስል አብዛኛውን ጊዜ ይሞታሉ።

- ኢየሱስ ከተገረፈ በኋላ ወታደሮቹ አፌዙበት።

## ማርቆስ 15፡16-20

16- ወታደሮቹ ፕራይቶሪዮን ወደ ተባለ ወደ ገዡ ግቢ ወሰዱት፤
ሰራዊቱንም ሁሉ በአንድነት ሰበሰቡ።
17- ቀይ ልብስም አለበሱት፤ የእሾኽ አክሊል ጐንጉነው በራሱ ላይ
ደፉበት።
18- ከዚያም፥ «የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን!»
ኢያሉ እጅ ነሡት፤
19- ራሱንም በበትር መቱት፤ ተፉበትም፤ ተንበርክከውም
ሰገዱለት።
20- ካፌዙበት በኋላም ቀዩን ልብስ ገፈፉት፤ የገዛ ልብሱን
አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።

- ወታደሮቹ ኢየሱስን መቱት፤ ተፉበትም።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው አዳኙ ተመታ ተተፋበትም።

- ሰዎች ነገሥታትን ለማክበር በፊታቸው እንደሚንበረከኩት ወታደሮች በኢየሱስ ላይ ለማፌዝ ሲሉ ተንበረከኩለት።

- ነገሥታት ቀይ ልብስ እንደሚለብሱ ወታደሮቹ ኢየሱስን ቀይ ልብስ በማልበስ አፌዙበት።

- ነገሥታት የወርቅ ዘውዶችን በራሳቸው ላይ እንደሚያደርጉ ወታደሮቹ በኢየሱስ ራስ ላይ የእሾኽ አክሊል በማድረግ አፌዙበት።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያት አማካይነት እንደተናገረው አዳኙ ተፌዘበት።

- የእሾኽ አክሊል የምን ምልክት ነበር?



- እግዚአብሔር አብ ስለ እኛ ኃጢአት ኢየሱስን እየቀጣው ስለ ነበር በመስቀል ላይ ተወው።

- በዔድን የአትክልት ስፍራ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር እንዳይበሉ ካዘዛቸው የዛፍ ፍሬ ከበሉ ምን ይደርስባችዋል አለ?

- ይሞታሉ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩ ከእግዚአብሔር በመለየት ሞቱ።

- አሁን ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ተለየ።

## ማርቆስ 15፡35-36

35- በዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳንዶቹ ይህን ሲሰሙ፥ «ኤልያስን
ይጣራል» አሉ።
36- ከዚያም አንድ ሰው ፈጥኖ ሄዶ የሆመጠጠ የወይን ጠጅ
በሰፍነግ ነከረ፤ በዘንግም ሰክቶ እንዲጠጣው ለኢየሱስ አቀረበለት። ከዚያም፥
«ተዉት፤ እስቲ ኤልያስ መጥቶ ሲያወርደው እናያለን» አለ።

- ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሚሞትበት ጊዜ ይመለከቱ የነበሩት ሰዎች ኢየሱስ ኤልያስን የሚጠራ መሰላቸው።

- ኢየሱስ ኤልያስን እየጠራው አልነበረም።

- ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አብ እየጮኸ ነበር።

- ኢየሱስ ወደ ኢግዚአብሔር አብ የጮኸው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን መተው አሰቃቂ ቅጣት ስለ ነበር ነው።

33- ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።

- በምድር ሁሉ ላይ ለሦስት ሰዓት ያህል ድቅድቅ ጨለማ የሆነው ለምን ነበር?

- የሦስት ሰዓት ጨለማ ምልክት ነበር።

- በምድር ሁሉ ላይ የነበረው የሦስት ሰዓት ጨለማ የምን ምልክት ነበር?

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን በመስቀል ላይ መተውን የሚያሳይ ምልክት ነበር።

ማርቆስ 15፡34

34- በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ፥ «ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ?» ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?» ማለት ነው።

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን በመስቀል ላይ በተወው ጊዜ ኢየሱስ ጮኸ።

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን በመስቀል ላይ ለምን ተወው?

- ኢየሱስ የሰራው ስሕተት ነበር?

- አልነበረም።

- ታዲያ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን የተወው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን የተወው ስለ እናንተ ስለ እኔና ስለ ሰዎች ሁሉ ኃጢአት እየቀጣው ስለ ነበር ነው።



- የእሾኽ አክሊል የእግዚአብሔር እርግማን ምልክት ነበር።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔር ምድርን በመርገም ምድር እሾኽ እንደሚበቅልባት ተናገረ።

- ወታደሮቹ በኢየሱስ ራስ ላይ የእሾኽ አክሊል ማድረጋቸው የምን ምልክት ነበር?

- ኢየሱስ የእግዚአብሔርን እርግማን መሸከሙን የሚያሳይ ምልክት ነበር።

ማርቆስ 15:21-22

21- የአሌክሳንድሮስና የሩፎስ አባት ስምዖን የተባለ አንድ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ መስቀሉን እንዲሸከም አስገደዱት።
22- ከዚያም ኢየሱስን፥ ትርጉሙ «የራስ ቅል ስፍራ» ወደ ተባለ ወደ ጎልጎታ ወሰዱት።

- ከዚያም ወታደሮቹ ኢየሱስን ለመስቀል ጎልጎታ ወደ ተባለው ከኢየሩሳሌም ውጭ ወደሚገኝ ኮረብታ ወሰዱት።

- በኮረብታው ላይ ወታደሮቹ መስቀሉን መሬት ላይ አድርገው ኢሱስን በመስቀሉ ላይ አጋደሙት።

- ከዚያም ወታደሮቹ የኢየሱስን እጆች በመስቀሉ በላይ በኩል እግሮቹን ደግሞ በመስቀሉ ግርጌ በምስማር ቸነከሯቸው።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው የአዳኙ እጆችና እግሮች ተበሱ።

- ወታደሮቹ ከቸነከሩ በኋላ ኢየሱስ የተቸነከረበትን መስቀል ቀጥ አድርገው አቆሙት።

- ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የነገረውን ታስታውሳላችሁ?

- ኢየሱስ “ሰዎች እንዲድኑ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን በእንጨት ላይ እንደሰቀለ ሁሉ ሰዎች ይድኑ ዘንድ አዳኙ መሰቀል አለበት” ብሏል።

ማርቆስ 15፡23-24

23- ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅም ሰጡት፤ እርሱ ግን አልተቀበለም።
24- ከዚያም ሰቀሉት፤ እያንዳንዱም ምን እንደሚደርሰው ለማወቅ ዕጣ ተጣጥለው ልብሱን ተከፋፈሉ።

- አንዳንድ ሴቶች ሕመም ማስታገሻ ይሆነው ዘንድ ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ ለኢየሱስ ሰጡት ኢየሱስ ግን አልተቀበለም።

- ኢየሱስን በመስቀል ላይ የቸነከሩት ወታደሮች ልብሱን ለመከፋፈል ዕጣ ተጣጣሉ።

- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው ሰዎች የአዳኙን ልብስ በዕጣ ተከፋፈሉ።

ማርቆስ 15፡25-27

25- ሲሰቅሉትም ጊዜው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ነበረ።
26- የክሱ ጽሑፍም፥ «የአይሁድ ንጉሥ» የሚል ነበር።
27- ከእርሱም ጋር ሁለት ወንበዴዎችን አንዱን በቀኙ አንዱን በግራው ሰቀሉ።

- ሌሎች ሁለት ሰዎች አንዱ በቀኝ አንዱም በግራ ከኢየሱስ ጋር ተሰቀሉ።

- ሁለቱም ክፉ ሰዎች ነበሩ።



- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረው አዳኙ ከክፉ ሰዎች ጋር ተገደለ።

ማርቆስ 15፡29-32

29- በመንገድ የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ የስድብ ናዳ በማውረድ እንዲህ ይሉት ነበር፦ «እዬ! ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስት ቀን የምትሠራ አንተ ነህ፤
30- እስቲ አሁን ከመስቀል ውረድና ራስህን አድን።»
31- እንዲሁም የካህናት አለቆችና ጸሐፍት በማሾፍ እርስ በርሳቸው እንዲህ አሉ፦ «ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አልቻለም።
32- አይተን እናምን ዘንድ ይህ ክርስቶስ፥ ይህ የእስራኤል ንጉሥ፥ እስቲ ከመስቀል ይውረድ።» ከእርሱ ጋር የተሰቀሉትም እንደዚሁ የስድብ ናዳ ያወርዱበት ነበር።

- ኢየሱስ አይሁዶች ቤተ መቅደሱን ቢያፈርሱት እርሱ በሦስተኛው ቀን እንደሚያነሣው ተናግሮ ነበር።

- ኢየሱስ የተናገረው አይሁዶች በኢየሩሳሌም ስለ ገነቡት የድንጋይ ቤተ መቅደስ ነበር?

- አልነበረም።

- ኢየሱስ የተናገረው ስለ የትኛው ቤተ መቅደስ ነበር?

- ኢየሱስ የተናገረው ስለ ራሱ ሰውነት ነበር።

- ኢየሱስ የተናገረው አይሁዶች እርሱን በመስቀል ቢያጠፉትም በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ነበር።

ማርቆስ 15፡33